# ከተገለጡት የተደበቁት ተሻሉ

ታረቀኝ ሙጨ

ማሳሰቢያ፤ ይህ ጽሑፍ 4 ገጽ ከሩብ አካባቢ ነው፡፡ ረጂም ጽሑፍ ማንበብ እሚወዱ ብቻ እንዲያነቡት ይመከራል፤ ለስልቹዎች ስላልታሰበ በርዝማኔው ምክንያት አንዳችም ስድብ የማላስተናግድ መሆኔን ከወዲሁ አሳስባለሁ፡፡

**መቅድም አንድ**

እኛ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል የነበረው ጨካኙና ሀገር ወዳዱ የደርግና አሁን ያለው አረመኔና ሀገር አፍራሹ የወያኔ መንግሥታት ሲያንሱን ነው፡፡ እየኖርነው ያለነው የሰቆቃና የግፍ ሕይወትም ሲያንሰን ነው፡፡ እንደጨው ዘር በዓለም ዙሪያ በስደት መበተናችን ሲያንሰን ነው፡፡ ከአንድ ምዕተ ዓመት በማይበልጥ ያሳለፍነው ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ መጠጊያቸውና ከደረቁቻ በረሃማ መሬት ማምለጫቸው ወደነበሩ የዐረብ ሀገራት ሴቶችና ወንዶች ልጆቻችን ለግርድናና እሽክርና አስከፊ ሕይወት መዳረጋቸው ሲያንሰን ነው፡፡ ወርቅ ላይ ተቀምጠን በምቀኝነትና የርስ በርስ ቁርቋሶ ተጠምደን፣ በኋላ ቀር ዳፍንታዊ መንጦላዕት ዐይናችንን በመጀቦን ከእምቅድመ ዓለም የሥልጣኔ ማማ ተሽቀንጥረን ወርደን፣ እኛ ያኔ የነበርነው ከእነሱ ያኔ ካልነበሩት የአሁናቸው ግርጌ መቀመጥም አቅቶን በቁማችን እንጦርጦስ መውረዳችን የሚገባን እንጂ የሚያንስብን አይደለንም፡፡ ነባሮቹ ሃይማኖታዊና ባህላዊ መልካም ምግባሮች ድራሻቸው ጠፍቶ ብኩን የሃይማኖት እረኞችና በገሃድ መብታቸውን የሚጠይቁ ግብረ ሶዳማውያን ዜጎች እየበዙልን መምጣታቸው የኩራታችን ፈርጦች በመሆናቸው እሰዬው ነው፡፡ እኛ በርሀብና በርዛት አለንጋዎች እየተገረፍን ጥቂቶችን በደቂቃዎች ውስጥ ከትቢያ አንስተን ሚሊዮነሮች ማድረጋችን ሲያንሰን ነው፡፡ ጭንቅላታቸው በምቀኝነት፣ በቅናት፣ በቂም በቀልና በተንኮል የተሞላ እባብ ዜጎችን በሀገር ውስጥም በውጪውም ማፍራታችንና ፖለቲካችንን እንደልብ ተቆጣጥረው እንዲፈነጩበት በግላጭ መተዋችን የዕድገታችን ምልክት በመሆኑ እንደአንድ አኩሪ ገጽታችን ሆኖ በጊነስቡክ መዝገብ ሊሰፍርልን ይገባል፡፡ ለሀገርና ለወገን ከመቆርቆር ይልቅ ለታሪካዊ ጠላቶች ያጎበደደ ትውልድ አፍርቶ ለሥልጣን ማብቃትና በውጤቱም ሀገርንና ሕዝብን አንበጣ የወረረው የሰብል ማሣ ማድረግ ከአንድ ታሪካዊ ሕዝብ የሚጠበቅ በመሆኑ አሁንም ልንኮራ ይገባናል፡፡ ዓለም የናቃቸውን የጎሣና የዘውግ ልዩነቶችን እኛ እንደአዲስ አንስተን እርስ በርስ እየተራኮትን ሌላውን ዓለም በተለይም አውሮፓንና አሜሪካንን እያስቀናን በመሆናችን ደስ ይበለን፡፡ ወዳጆቻችን እነቻይናና አሜሪካም ሃሤትን ያድርጉ፡፡...

**መቅድም ሁለት**

የዓለም ዕድገትና ሥልጣኔ እንደስከዛሬው ባልተስፋፋበት ቀደም ባለ አንድ ወቅት ነው፡፡ አንድ አሜሪካዊ፣ አንድ ራሺያዊና አንድ ኢትዮጵያዊ እግዚአብሔር ዘንድ ቀርበው ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ጥያቄው፡- "ሀገሬ መቼ ነው አድጋና በልጽጋ የሕዝቧ የኩራት ምንጭ እምትሆነው?" የሚል ነው፡፡ መጀመሪያ አሜሪካዊው ወደቢሮ ይገባና ይህንኑ ጥያቄ በራሱ ቋንቋ ያቀርባል፡፡ እግዜሩም እንዲህ በጥሞና ካዳመጠ በኋላ እንዲህ ይለዋል፤"የዛሬ ሃምሣ ዓመት ገደማ!" አሜሪካዊው ተደስቶ ይወጣል፡፡ ራሺያዊው ይቀጥላል፡፡ ፈጣሪም "ከመቶ ሃምሳ ዓመት በኋላ!" ይለውና ሩስኪው እንደመከፋት ብሎ ይወጣል፡፡ የኢትዮጵያዊው ተራ ይደርስና ጥያቄውን ሊያቀርብ የቢሮውን በር ከፈት ከማድረጉ የህበሻው ጥያቄ ምን እንደሆነ አስቀድሞ የገባው እግዚአብሔር ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት እዬዬውን ይለቀዋል - አለውም "ያንተ ሀገር ኢትዮጵያ አድጋ የምትታይበትን ዘመን እኔ ራሴም አልደርስበትም የኔ ልጅ!"

**መንስኤ ነገር**

አንድ ቅዳሜ...ከቤተሰብ ጥየቃ መልስ እንደወትሮው ተሰባስበን ምግብ በምንቋደስበት ቦታ አንድ ሰው አልተገኘም፡፡ የሆነ ነገር ቅር ሲለኝ ዙሪያ ገባውን ባይኔ ቃኘሁ፡፡



EthioLion.com

"ጃክስ?" ስል ጠየቅሁት፡፡
ፋሲል፣ ዶክተር ያዕቆብን በርቀት አመላከተኝ፡፡ ከእስር ግቢያችን ዋና መግቢያ በር አጠገብ ውሃ ልክ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል፡፡ ክርኖቹን ጉልበቱ ላይ አስደግፎ በእጆቹ መዳፎች ጉንጮቹን አንተርሶ አቀርቅሮ መሬት መሬት ያያል፡፡ አቀማመጡ የመከፋት ስሜት ውስጥ እንዳለ ያሳብቃል፡፡

"ምን ሆኗል?"

"ምን እባክህ" አለ ፋሲል "እዚህ ትልቅ እምትለው አንዳንዱ ሰው በድርጊቱ የትንሽ ትንሽ ይሆንብሃል፡፡ ይቀልብሃል፡፡ በተለይ ደግሞ እገሌ..." አለኝ አጠገባችን በሚገኘው ማዕድ ዙሪያ ክብ ሠርተው ከሚመገቡት የቅንጅት አመራሮች መሃል አንዱን በአገጩ እየጠቆመኝ፡፡

"ዛሬ ደግሞ ምን ተከሰተ?"

"ከእርሱ ቤተሰቦች መካከል አንዱ ዛሬ ለዶክተር ያዕቆብ ስጦታ ይዞ መጥቶ ነበርና ሰጠው፡፡ ይሄኔ ‹ተቀበለው!› ብሎ አዘዘ፡፡ ጠያቂው ምንተፍረቱን ‹ይቅርታ፣ ለሌላ ሰው ይገዤ የመጣሁትን ስጦታ ነው የሰጠሁህ› ብሎ ከዶክተር ያዕቆብ መልሶ ተቀበለው፡፡ ወዲያው ‹ወስደህ ለዶክተር እከሌ ስጠው!› ብሎ አዘዘው፡፡ ጠያቂውም እንደተባለው አደረገ፡፡"

"ከአንዱ ነጥቆ ለአንዱ?ለምን?" ጥያቄዬ የመገረም ዓይነት ነበር፡፡

"እርሱና ዶክተር ያዕቆብ በሽምግልና ጉዳይ የአመለካከት ልዩነት እንዳላቸው ታውቃለህ አይደል? የአመለካከት ልዩነቱ እስከመኮራረፍ ዘልቋል፡፡ ስለዚህ ከእርሱ አመለካከት ጋር ለተስማማው ለዶር. እከሌ እንዲሰጥ አደረገ፡፡ ጃክ የተናደደውና ያዘነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡" አለኝ፡፡

" ግን የእርሱ ቤተሰብ ለዶር. ያዕቆብ ያመጣው ስጦታ ምን ነበር?"

"የአንገት ሹራብ(scarf)"

በዚያች ቅጽበት አንዳች የሀፍረት ስሜት ወረረኝ፡፡ ተደረገ የተባለው ነገር ስለመደረጉ ‹ከባለቤቱ አፍ› ስሰማ ሀፍረቴ ወደ ሐዘን ተለወጠ፡፡

... ቤተሰብ በመካከላችን የአቋም ልዩነት መከሰቱን አያውቅም፡፡ በርግጥ የአመለካከት ልዩነት የነበረ፣ ያለና የሚኖርም ነው፡፡ የሃሳብ ልዩነት መከሰት እንኳንስ ለአንድ ፖለቲከኛ ለሌላውም የሚገርምና የሚደንቅ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በአመለካከት ተለየኝ ብሎ፣ ቅሬታን በቤተሰብ ስጦታ አስታክኮ ማንፀባረቅ፣ ከአንድ ፖለቲከኛ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ...

"አሁን እነዚህ ናቸው ቅንጅትን እሚያህል ፓርቲ ሲመሩ የነበሩት?" እላለሁ በግዴለሽነት ስሜት፡፡ ማንም ቢሰማኝ ግድ አልነበረኝም፡፡ "ብቻ ከእስር ቤት የመውጣት ዕድል ላግኝ እንጂ ይሄን ጉዳቸውን ሳላወጣው አልቀርም፡፡ እነዚህ ሰዎች የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም የቤተሰብ ማኅበር መምራት እንደማይችሉ ከመናገር ወደኋላ አልልም፡፡" እላለሁ፡፡ [ወሰን - እንኳን ተሣካልህ!]
ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን (2004) የቃሊቲ ምሥጢሮች (ገጽ 127-129፣ መስመር ከራሴ) (harawosen@gmail.com)

"ስብሰባው እንዲህና እንዲያ እያለ አስተያየት የተሰነዘረበትና በ30 ደቂቃ ውስጥ የተጠናቀቀ ቢሆንም እኔን እጅግ በጣም የገረመኝ አንዳችም ጠብ የሚል ቁም ነገር ሳይናገርበት አብዛኛውን ደቂቃ የፈጀው ተስፋዬ ታሪኩ መሆኑ ነው፡፡ በእስር ቤት ሕይወት ውስጥ ካገኘኋቸው ሰዎች መሃል እጅግ በጣም የሚያሳዝንህና የምታዝንለት፣

የሚያበሳጭህና የምትበሳጭበት፣ የምትገረምበትና የምትገረምለት፣ የሚያሣፍርህና የምታፍርለት፣ የሚያስቅህና የምትስቅበት... አንድ ሰው ጥራ ብባል የማስቀድመው ተስፋዬን ነው፡፡” (ዝኒከማሁ፣ ገጽ 104)

**ማጠቃለያ አንድ**

እኛ እንዲህ ነን እንግዲህ፡፡ የኛች ከምንላቸው ውስጥም ‹ጥቂቶቹ› እንዲህ መሆናቸው ነው፡፡ ነገራችን ሁሉ “ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ!” የሆነብን የተስፋቢሶች ተስፈኞች፡፡ ቢከፍቱ ተልባ፡፡ ሰው መሳይ በሸንጎዎች፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ተዋንያን “ድመት መንኩሣ ዐመሏን አትረሣ” ዓይነት አሣዛኝ ፍጡራን ነን፡፡ ትንሹም ዳቦ ትልቁም ዳቦ ሁሉም ተያይዞ ሊጥ የሆነበት አስገራሚ ዘመን! ማንም አባ ደፋር ከነማይምነትና ያልተሞረደ ዕድፋም ስብዕናው ዘገደው እሚልበት የፖለቲካ ባዑር የሠራን አስደናቂ ሕዝብ - እንደሕዝብ! በግሩም ልብስ የተጀቦኑ አስፈሪና አሣፋሪ ጉዶች፣ በሚያማምሩ ‹አቶ›ን ፋቂ ትምህርታዊና ወታደራዊ ቅጽሎች የተዋጁና በነዚያ አላፊና ብል እሚበላቸው ማዕረጋት በድህ ወገናቸው ላይ የሚኮፈሱ ማይማን፣ በአንደበተ ርቱዕነት የማይታሙ ሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሯቸው እየቀፄ ሲታይ ግን ከመርዘማ ንጥረ ነገር የተዋቀረ አሉቧልተኞች... የተሰገሰጉበት የፖለቲካ ሥሪት ባለቤት የሆንን አሣዛኝ ዜጎች - ኢትዮጵያውያን፡፡ አቤት የገባንት አዘቅት!!

የወሰንሰገድን መጽሐፍ ሳነብ ዕንባ እየተናነቀኝ ነው የጨረስኩት፡፡ በኢትዮጵያዊነቴ እንደዚህ ቅጽበት አፍሬ አላውቅም፡፡ አንዳንዶች በጣም ዘገዬህ እንደምትሉኝ አላጣሁትም፡፡ የኛ ነገር ተከድኖ ይብሰል እንጂ ሁሉን ካወሱት የሚጣል እንጂ የሚነሣ የለውም፡፡ ለዚህም ነው ከአንዱ ማጥና አረንቋ ወጣን ስንል ወደባሰበት ሌላ ማጥና አረንቋ የምንቀረቀረው፡፡ የሾተላዩ ሠይፍ ስለቱ ሊበርድልን ቀርቶ ከቀን ቀን እየተሞረደና ይበልጥ እዬሰላ ቀልቶ ሊፈጀን ነው፡፡ መጨረሻውን ያሳምርልን፡፡

ግንቦት ወር ውስጥ ነው የምንገኘው፡፡ ግንቦት ለኢትዮጵያ ብዙም የምትመች አይደለችም፡፡ ግንቦት 8/81ዓ.ም ኢትዮጵያ ብዙ የለፋችባቸው ከፍተኛና የመስመር መኮንኖች መቻቻልንና ምሕረትን በማያውቀው የወቅቱ አምባገነን መሪ (ባይሞትም ነፍሱን ይማር) መንግሥቱ ኃ/ማርያም በይስሙላ ፍርድና አለፍርድ እንዲጨፈጨፉ ምክንያት ሆነ፡፡ በሁለተኛው ዓመት ግንቦት 20/83 የነዮዲት ጉዲትና የነግራኝ አህመድ የመንፈስ ውልድ የሆነው የምዕራባውያን አሻንጉሊት መንግሥት ‹ኢሕአዴግ›በሚለው የማስመሰያ ስመ ጥምቀት የውጪና የውስጥ መርዘቀባዮቹ ባደረጉለት ሁለገብ ረድኤት ከጫካ ወጥቶ አዲስ አበባ ላይ ተተከለ፡፡ ግንቦት 7/97 የእንቁልልጭ ዴሞክራሲ ብቅ ብሎ አጓጉቶንና የበርካታ ዜጎቻችንን ደም በጭዳነት በከንቱ አፍስሶ ላይመለስ ሄደ፡፡ የዚያ የተረገመ ልዩ ግንቦት ጦስ ጥንቡስ እስካሁን አልለቀን ብሎ ይሄውና ኑሯችንን ክፉኛ አመሰቃቅሎት ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ሆነን በመንፈስም በሥጋም እዬተንጠራወዝን እንገኛለን፡፡ ግንቦት ወር በሌላ መልክም ይሄን መሰሉ ገደቢስነቷ ቢፈለግ አይጠፋም፡፡ ለነገሩ የአሁኑን አያድርገውና ሠርግ እንኳን በግንቦት ወር አይደረግም ነበር - ገደቢስ ወር ነው ተብሎ ስለሚታመን፡፡ ለወደፊቱ ግን ኢዮብ የተወለደባትን ዕለት ከቀናት ሁሉ ለይቶ እንደረገማት ሁሉ እኛም ይህችን እርጉምት ወርኃ ግንቦት ለዳግመኛው እንዳናያት ቀናቱን ወደተቀሩቱ ብንበትናት ሳይሻለን አይቀርም፡፡ ምልኪዋ አልበጀንምና፡፡

**ማጠቃለያ ሁለት**

ለሕዝብ ለውጥ ሊያመጡ እሚመስሉ ጅምሮዎች ለምን ይከሽፋሉ? ጥበበ ወርቅዬ የሚባለው ዘፋኝ ይመስለኛል፡ - “አሁን ገና ገባኝ” እያለ እሚያቀነቅናት ዘፈን አለችው፡፡ ወጣቶች አርሙኝ፡፡ አዎ፣ አሁን ገና ነው በጣም የገባኝ ለምን እንደሚከሽፉብን፡፡ ወደፖለቲካው እሚገቡ አብዛኞቹ ሰዎች እንደ ልደቱ አያሌው ያሉ በአፋቸው ጤፍ እሚቆሉ ተራ የፖለቲካ ቁማር ቆማሪ ሌቦች፣ አጭበርባሪዎች፣ አስመሳዮች፣ ለሥልጣንና ለዝና ሟቾች፣ የስመጥርነት ምርኮኞች፣ ዋና ዓላማቸውን ሀብትና ገንዘብ ያደረጉ ስግብግቦች፣ በጭቁኖች ሞት ተረማምደው የሁሉም ነገር ጣርያ ላይ ቁብ ማለት እሚፈልጉ የማኪያቬሊ ደቀ መዛሙርት ስለሆኑ ነው፡፡ ለሕዝብ አስባለሁ እሚልና የሕዝብን አመኔታ አግኝቶ በሺዎች ደም የበለፀገ የፖለቲካ ስብዕና ባለቤት የሆነ ሰው በተራ ቅያሜ ተነሳስቶ በስጦታ የመጣን የዘመዱን የ10 ብር ያንገት ሽርጥ (ስካርፍ) ከመጣለት ሰው ቀምቶ ለሌላ አይሰጥም ነበር - ሰው ቢሆን፤ በሺዎች ደም አንቱታን ያገኘ የፖለቲካ ሰው ጎረቤት ሀገር ስደተኞች ጣቢያ ለሚገኙ ልጆቹ አፊዳቪት ወይም የፖለቲካ ጥገኝነት እስኪያገኙለት ድረስ በእስር እንዲቆይ ብሎ የይቅርታ ተብዬውን ፊርማ “እባካችሁ አንፈርም” ብሎ ታሣሪ ጓደኞቹን ባላወከ ነበር፡፡ (የወሰንሰገድን መጽሐፍ ያነቧል) ይህ አድሮ

ቃሪያነታችን ነው እንግዲህ ከዚህ መጣጥፍ መግቢያ ጀምሮ በንዴት እያንጨረጨረ እዚህ ድረስ እንድዘልቅ ያደረገኝ፤ እኔም እንዳቅሚቲ እናገራለሁ! ምኑ ሲቀርብኝ? ፒ! “ቂጣ ቢያንቅ በውሃ ይዋጣል፤ ውሃ ቢያንቅ በምን ይዋጣል?” በቅንጅት ስም የስሙ ግነት ሰማየ ሰማያት የደረሰ ሰው እንደሕጻን ሲያደርገውና እንዲያውም ከሕጻንነትም በወረደ እንደለየለት ዕብድና ወፈፌ ገና ባልተገኘ ሥልጣንና ወንበር እንዲህ ከሆነ እኛ እዚህ ግቡ እማንባለው ወፍዘራሾች አንሻልም ትላላችሁ? “የዘገነም አዘነ፤ ያልዘገነም አዘነ” እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር እምንም ውስጥ ሳይገቡ አንጋጥጠው ብቻ በኤሎሄ የሚኖሩ ምሥኪን ዜጎች ከነዚህ ቅሌታም ‹ትላልቅ› ሰዎች በእጅጉ የተከበረ ዋጋ አላቸው ብዬ በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡፡ ለነገሩ የሰው ሥራው ከቤቱ ውጪ ነው እሚያድር፡፡ እናም የአንዳንዶቹን አስጸያፊ ተግባር ዱሮውንም እንሰማ ነበር፡፡ ነገር ግን ወላድ በድባብ ትሂድ በውስጡ የነበሩና ሁሉን የታዘቡ እንደወሰንሰገድ ያሉ ደፋር ወጣቶች ጉዳቸውን ዘክዝከው አሳዩን - ዘር ይውጣላቸው፤ ቢስም አይይብንና ፈጣሪ በነሱ ይካሰን ፡፡ እናም የማን ማንነት አሁን ወለል ብሎ ታየን፡፡ በየለውጥ ምዕራፎች የሚመጡ ልጆቻችን ሲያሳፍሩን እንጂ ሲያኮሩን አናይም፡፡ የግንቦት ስምንቶቹ ምሥኪኑ ሕዝብ እየተራበ ዊስኪና ጮማ ሲቆርጡ ቆይተው፣ አንዳንዶቹ በየቤታቸው ስንትና ስንት የጤፍና የዊስኪ ቁልል የተገኘባቸው፣ መንግሥቱ ኃ/ማርያምን የመሰለ ጭራቅ አስቀምጠው ባልተጨበጠ ሥልጣን የተገዳደሉ ሞኞች… ሆነው ተገኙ፡፡ እናም ፈጣሪ እነሱን ባይፈቅድልን ይሆናል አከሸፈው፡፡ የግንቦት ሃያዎቹ በርግጥ ወንበሩን ይዘውታል ግን ያዋጁን በጆሮ ነውና ልለፈው፡፡ የግንቦት ሰባት 97ዓ.ም ደግሞ ቆየት ብለን እንዳየነው እስር ቤት ውስጥ ተቀምጦ እስከመሹዋሹዋም የደረሱ ቂሎች ወይም ዶን ኪሾቶች የሞሉበት፣ ብረት ሲመስሉን ኩበት ሆነው ያገኘናቸው ሰዎችን የታዘብንበትና ምናልባትም ሥልጣኑ በነዚህን መሰል ሰዎች እጅ ቢገባ ኖሮ እንደማንጠቀም አስቦ ይሆናል ፈጣሪ አሳይቶ የነሣን፡፡ ምሥጢሩ ረቂቅ ነው፡፡ …

ልብ ካለን ከእንግዲህ ማንም እንዲያጭበረብረን መፍቀድ የለብንም፡፡ ለወትሮው የሞኝ ብልኀነት አንዴ ነበር የሚያሞኝ - ዛሬ ዛሬ ግን ዕድሜ ልክ ሊሆን የቃጣው ይመስላል፡፡ ለዚህም ነው ሕዝቡ በአሁኑ ወቅት ፀጥ ረጭ ያለው፤ ማንን ይመን? ማንንና እንዴትስ ይጠጋ? ያበራሽን ጠባሳ እሚያክም ሳይገኝ ማን ነው ደፍሮ በእሳት እሚጫወት? ‹እውነተኛው ሙዜ ተገኝቶ ሙሽራዋን ሳያዝላት› እንዴት ተደርጎ ሃይ ሎጋው ይባል? ሙሽሪትስ ስንት ጊዜ ትታለል? ፈረንጅ በዚህ ዓይነቱ አስጨናቂ አጋጣሚ “Let us wait until the cat jumps.” የሚለው ወዶ አይደለም፡፡ እኛም እኮ ‹አትቀደም› ‹ሰኞን አለመሆን ነው› እያልን ነው ብልጥ ለብልጥ ዐይናችንን ስንበለጥጥ ጀምበር ልትጠልቅ የተዳረሰችውና ለተምቾቹም ምቹ ሆነን የቀረነው፡፡ ብናውቅበት በሕግ አምላክ የማለት መብቱ የኛው ነበር፡፡ … የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም፡፡ ከእንግዲህ ምን ሲቀርብን? ያመኑት ፈረስ ሁሉ በደንደስ ሲጥል እያየን? ሀገራችን እንዴቱን ያህል ብትረገም ይሆን ግን የልደቱአዊ ዋልጌዎች ማምረቻ ፋብሪካ ሆና የቀረችው? ለምንድነው የወላድ መካን የሆነችው? የሰው አባባል ልዋስና ቆንጆዎቹ ወዴት አሉ? ወይንስ ገና አልተወለዱም? በእርግጥ ይህም ዘመን እንደቀደምቱ የመከራ ዘመናት አልፎ ልጆቻችን የእፎይታ ጊዜ ያገኙልን ይሆን? ዕድሜ ሰጥቶን ማየት ብንችል በበኩሌ እንደገና የመፈጠር ያህል እቆጥረዋለሁ፡፡ ሁሉን ነገር ማድረግ የማይሳነው አምላክ ይስማን፡፡

**በተለይ ለወጣቶች፡-**

ከእኛ ከ‹ትላልቆች› ተማሩ፡፡ ካቆየንላችሁ የምቀኝነትና የትንሽነት ስብዕና በአፋጣኝ ውጡ፡፡ በዛሬ ዘመን ትልቅ እሚባል ሰው ማግኘት ከባድ እየሆነና እናንተም በአርአያነት እምትከተሉት ሰው እየጠፋ በመሆኑ የቀድሞዎቹን መልካም ሰዎች አብነት ከመጻሕፍት እያነበባችሁ ራሳችሁን አንጹ፡፡ እርግጥ ነው አሁንም ቢሆን መጠናቸው አንሶ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሊፈጥሩት እሚችሉት አወንታዊ ተፅዕኖ ጎልቶ ሊወጣ ባለመቻሉ እንጂ እንደነዶክተር ኃይሉ አርአያና ዶክተር ዳኛቸው አሰፋን የመሳሰሉ እውነተኛ የሀገር ተቆርቋሪ ምሁራን በውስጥም በውጪም አሉን - ጨርሶ አይበድልም፡፡ (የወሰንሰገድን መጽሐፍ ያነቧል) በዛሬ ዘመን የምታዩትን ትልቅ ሰው የዕድሜ በረከቱን እንጂ ተግባሩን እምብዝም አትመኙ፡፡ ከሁሉም ከሁሉም መልካም መጻሕፍትን እየመረጣችሁ አንብቡ፡፡ በመጻሕፍት ራሳችሁን አሳድጉ፤ ብዙዎቻችሁን ስታዘብ ሕይወታችሁ ሩጫ የበዛበት ከመሆኑ አንጻር ሰፋ ያለ ነገርን በጥልቀት ከማንበብ የራቃችሁ ትመስሉኛላችሁ፡፡ ያንዳንዶቻችሁን የቋንቋ አጠቃቀም ስታዘብ ደግሞ ብዙ ማንበብ እንደሚኖርባችሁ እየተረዳሁ መጥቻለሁ፡፡ ይህን ስል ተስፋ ሰጪ ወጣት ምሁራን ዜጎች መኖራችሁን ዘንግቼው አይደለም፤ ነገር ግን ገና ብዙ እንደሚቀረን ይሰማኛል፡፡ ያለ ነገር ወዴትም አይኼድምና ባለን ነገር ከመኮፈስ ይልቅ ለመጨመር መጣር የትልቅ ስብዕና ዓይነተኛ ምልክት ነው፡፡ የንባብ ትሩፋት እውነተኛ ማንነትን ያስገኛልና ጓደኛችሁ መጽሐፍ ይሁን፡፡ በመሠረቱ ዘመናዊ ባህል ጥሩ ነው፤ ዘመናዊ መሆንም ጥሩ

EthioLion.Com

ነው፡፡ ነገር ግን በዘመናዊነት ስም በነፈሰው ንፋስ ሁሉ አትወሰዱ፡፡ ሀገራችሁ ያለ ተረካቢ እንዳትቀር እኛን ታላላቆቻችሁን- ዕድሜችንን በከንቱ ያሳለፍነውን የትውልድ እርጉማንን ሳትመለከቱ በንባብና በሕይወት ገጠመኝ በምታዳብሩት ዕውቀትና ግንዛቤ የጥበብ ሰዎች ሁኑ፡፡ ሁሉም ያልፋል፡፡ ነገር ግን የሚያልፈው በአዲሱ ሲተካ መጪው የእናንተ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ አለበለዚያ አሮጌ መጥፎ ነገር በአዲስ መጥፎ ነገር ሊተካ እንደሚችልም መረዳት ይኖርባችኋል፡፡ ዘመኑ የኀብስተ መና ሣይሆን የጥረትና የልፋት መሆኑን ልብ በሉ፡፡ በዛፍ ላይ የሚገኘን ጣፋጭ ፍሬ ሌላ ሰው አውርዶ እንዲያጎርሳችሁ ከጠበቃችሁ ሞኝነት ነው፡፡ አውራጅ እንኳን ቢኖር በእናንተና በዛፉ መካከል ያለው ርቀት የምትጠብቁትን ያህል ፍሬ እንድትጎርሱ ላያደርግ ይችላልና ሁልጊዜ ተራራው ወደእናንተ እንዲመጣ ከመጠበቅ ይልቅ እናንተም ወደተራራው እንደትሄዱ ዘመኑ ያስገድዳችኋል፡፡ ከእኛ የምትማሩት መልካም ነገር እምብዝም ያለ አይመስለኝም፡፡ እኛ ባስቀመጡን እማንገኝና በዘመናችን የሰይጣን መሣሪያ ወደ መሆን ያዘነበልን ምግባረ ጥፉዎች ነበርንና የተውንላችሁ ቅርስ እምብዝም የለም፡፡ የምንሸከመው ትልቁ የትምህርት ደረጃ ሰውን በከንቱና አለሥራው በሃሜት ከመቦጨቅና ከመጥላት እንደአፍላ ጎረምሣም ሰው እስኪታዘበን ድረስ ፀያፍ የዱርዬ ስድብ ከመወራወር አላዳነንም፡፡ ‹ተምሮ ላፈር› ማለት ይህን ዓይነቱን በቁሙ ‹መሃራ ለነፍሰ ገብሩ…› እሚያስብል ምሁር ተብዬ የሀገር ሸክም ነበር፡፡ ምክንያቱም ላይጠቀምበት ብዙ የሀገር ገንዘብና የራሱን ዕድሜ አለመላው ፈጅቷልና፡፡ ሲመረቅ የለበሰው ጥቁር ካባና መነሳነስም የሀዘን ጅማሮውን እንጂ ሀገሩንና ሕዝቡን ለመጥቀም ቃለ መሃላ መግባቱን በጭራሽ አያመለክትም፡፡ የምሁራን ደናቁርት የተሸከመች ብቸኛዋ ሀገር ኢትዮጵያችን መሆንዋን ተገንዝባችሁ አዳዲስና ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ ምሁራን ለመሆን ጣሩ፤ በእውነቱ ከወጣቱ ብዙ ይጠበቃል፡፡ ከገንዘብ አምልኮትም ባፋጣኝ ውጡ፡፡ ገንዘብ ወገንን ያስከዳል፤ሀገርን ያሸጣል፤ሃይማኖትን ያስክዳል፤ የኅሊናን ሚዛንም ያናጋል፡፡ እነመለስም ሆኑ ከነሱ በፊት የነበሩት መሪዎች ባብዛኛው እነዚህ በመሳሰሉ ችግሮች የተጠቁና የሀገር ስሜታቸውን የራስ ወዳድነት ብል የበላው ነበሩ፡፡… በተለይ በህክምናው ዘርፍ የተሰማራችሁ ባለሙያዎች ምሥኪን ወገናችሁን በቀናነትና በትጋት ማገልገል እንድትችሉ፣ አንዳንዶቻችሁም በፍቅረ ንዋይ ተማርካችሁ ከተዘፈቃችሁበት ጠርዝ የለቀቀ የገንዘብ አሰባሰብና ኢሥነ ምግባራዊ የሆነ የህክምና አሰጣጥ እንድትወጡ …እግዚአብሔር ይርዳችሁ፡፡

አስተያየት ካለዎ፤ tmuchie95@gmail.com

EthioLion.com